የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት

ልሣነ ህግ ጋዜጣ

24ኛ ዓመት ቁጥር153

አሶሳ
መጋቢት 1/2010 ዓ.ም

በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ክልል

ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ አዋጅ

ያንዱ ዋጋ ብር-----------

ፖ.ሳ.ቁ.፡ 293

**አዋጅ ቁጥር 153/2010 ዓ.ም**

**የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት የኅብረት ሥራ ማኅበራት ማደራጃና ማስፋፍያ ቢሮ ለማፍረስ የወጣ አዋጅ፤**

**ገጽ-----------------------**

በአዋጅ ቁጥር 20/1992 ዓ.ም የተቋቋመዉ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት የኅብረት ሥራ ማኅበራት ማደራጃና ማስፋፍያ ቢሮን በማፍረስ እንደገና በኤጀንሲ ደረጃ ማደራጀት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ክልል ምክር ቤት በተሻሻለዉ የክልሉ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3.1 በተሠጠዉ ሥልጣን መሠረት የሚከተለዉ ታዉጇል፡፡

**አንቀጽ 1**

**አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ የኅብረት ሥራ ማኅበራት ማደራጃና ማስፋፊያ ቢሮ ለማፍረስ የወጣ አዋጅ ቁጥር 153 /2010 ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ፡፡

**አንቀጽ 2**

**ስለማፍረስ**

በአዋጅ ቁጥር 20 /1992 ዓ.ም ተቋቋመዉ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት የኅብረት ሥራ ማኅበራት ማደራጃና ማስፋፍያ ቢሮ በዚህ አዋጅ ፈርሷል፡፡

**አንቀጽ 3**

**ስለ መብትና ግዴታዎች መተላለፍ**

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት የኅብረት ሥራ ማኅበራት ማደራጃና ማስፋፊያ ቢሮ መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለክልሉ የኅብረት ሥራ ማኅበራት ማደራጃና ማስፋፊያ ኤጀንሲ ተላልፈዋል፡፡

**አንቀጽ 4**

**አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ክልል ምክር ቤት ከፀደቀበት መጋቢት 1 ቀን 2010 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል ።

አሶሳ

መጋቢት 1 ቀን 2010 ዓ.ም

አሻድሊ ሃሰን አልአጅብ

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ፕሬዝዳንት